## መዳን የሚገኝበት መንገድ

አቅራቢ፦ ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)

ሐምሌ 5/2018

**ትምህርት 6፦** በኃጢአቱ ምክንያት የወደቀውን የሰው ዘር ለማዳን እግዚአብሔር ያዘጋጀው የመዳን መንገድ ይህ ነው።

የሰው ዘር ሁሉ ኃጢአተኛ ከሆነና በራሱ ጥረትና ችሎታ ምንም የኃጢአት እንከን የሌለበት በመሆን ከመርገምና ከዘላለም ሞት ማምለጥ ካልቻለ ያለው መፍትሄ ምንድነው?

እግዚአብሔር የፍቅርና የርህራሄ አምላክ በመሆኑ የሰው ዘር ሁሉ በኃጢአቱ ምክንያት የዘላለም አሰቃቂ ስቃይ ከመጠባበቅ ውጪ ምንም መፍትሔ እንደሌለው በማየቱ ያዘጋጀው **ብቸኛ የሚያድን መፍትሄ የሰውን ዘር ኃጢአት ውጤት የሆነው መርገምና የዘላለም ሞት ፍርድ ዕዳ ተቀብሎ በመሸከም ነጻ የሚያወጣ መስዋዕት አንድያ ልጁን አቀረበ። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ስለ እኛ ኃጢአት በእንጨት መስቀል ላይ እንደ መስዋዕት በግ ተሰውቶ መሰቃየቱና ደሙን ስለ እኛ በማፍሰስ መሞቱ ነው።** ስለዚህ ማንኛውም ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የከፈለው ታላቅ መስዋዕትነት የኔን ኃጢዓት በደሙ በማጠብ ሊያነጻኝ ነው በማለት ካመነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ያገኛል።

መዳን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የሚገኝ መሆኑን ከሚያረጋግጡ በርካታ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሉቃስ 1፡30-31፣ …[30] መልአኩም እንዲህ አላት፤ “ማርያም ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ።[31] እነሆ፣ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። … (በዕብራይስጥ የሹዋ/ኢየሱስ ማለት ሕዝቡን የሚያድን አዳኝ ማለት ነው)

**ማቴዎስ 1፡18-21፣** የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እንዲህ ነው፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። [19] እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ ነበርና ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት ስላልፈለገ በስውር ሊተዋት ወሰነ። [20] በዚህ ሐሳብ ሳለ፣ የጌታ መልአክ በሕልም ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው፤ “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ እጮኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፤ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና። [21] ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና።”

**ሉቃስ 2፡8-12፣** በዚያው አገር በሌሊት መንጋቸውን ሲጠብቁ በሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ። [9] የጌታም መልአክ ድንገት መጥቶ በአጠገባቸው ቆመ፤ የጌታም ክብር በዙሪያቸው አበራ፤ ታላቅም ፍርሀት ያዛቸው። [10] መልአኩ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች አምጥቼላችኋለሁና። [11] ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀን ተወልዶላችኋልና፤ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው። [12] ይህ ምልክት ይሁናችሁ፤ ሕፃን ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ።”

**ሐሥ 4፡9-12፣** ዛሬ ለዚህ ሽባ ሰው ስለ ተደረገው በጎ ሥራ፣ እንዴት እንደ ዳነ የምትጠይቁን ከሆነ፣ [10] እናንተ በሰቀላችሁት፣ እግዚአብሔር ግን ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መዳኑንና ፊታችሁ መቆሙን እናንተም ሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይህን

ይወቅ:: [11] እርሱም፣ "እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፣ የማእዘን ራስ የሆነው ድንጋይ' ነው:: [12] ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና::"

ሐሥ 10፥42-43፣"ለሕዝቡ እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታንም ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔር የሾመው እርሱ መሆኑን እንድንመሰክር እርሱ ራሱ አዘዘን፤ [43] በእርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል::"

"ሉቃ 19:9-10፣ [9] ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለ ሆነ፣ ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤ [10] ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው::"

**የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምኖ መቀበል**

**ሮሜ 3:21-26**፣ አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል:: [22] ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው:: ልዩነት የለም፤ [23] ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ [24] በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤ [25] በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቀርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው፤ [26] በአሁኑ ዘመን ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን፣ ለማሳየት ነው::

**ዮሐንስ 3:16-17**፣ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤ [17] እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው::

ዮሐ 14፥6፣ "ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::"

**ገላትያ 2፥16**፣ "ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ ሕግን በመጠበቅ እንደማይጸድቅ እናውቃለን:: ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን እንጸድቅ ዘንድ እኛም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል፤ ሕግን በመጠበቅ ማንም አይጸድቅምና::"

**ኤፌሶን 2:8-9**፣ በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ [9] ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤

ኤፌሶን 2:16-18፣ "ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው:: [17] መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፥ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ፤ [18] በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና::"

ገላትያ 5፥4 "በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል::"

ስለዚህ ከዚህ በላይ የሰፈሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ የሚያስረዱት በኃጢአት ምክንያት የወደቀው የሰው ዘር ኃጢአቱ ከሚያስከትልበት አስከፊ መዘዝ ሁሉ መዳን የሚችለው ጌታ ኢየሱስ አከናውኖ በጨረሰው እስከ መስቀል ሞት ድረስ በከፈለው እጅግ ታላቅ ዋጋና ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ነው በማመን ብቻ ነው፡፡

***መዳን/ድነት* (Salvation) *ማለት ምን ማለት ነው፡-***

እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ሲፈጥር ኃጢአት የሌለበት አድርጎ ፈጥሮት የነበረ ሆኖ ሳለ፣ ከጊዜ በኋላ ሰው እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ በመጣስ አትብላ ከተባለው ዛፍ ፍሬ ስለበላ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ ሆነ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከቃኤል ጀምሮ የሰው ኃጢአት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየበዛ ሄደ እንጂ በንስሃ ወደ እግዚአብሔር አሳብ አልተመለሰም፡፡ በዚህ ምክንያት የሰው ዘር፣ ለሥራ ሕግ፣ ለኃጢአት ባርነት፣ ለእርግማንና ለክፉ መናፍስት ተገዢ በመሆን የእግዚአብሔር ቁጣ ውጤት የሆነው የዘለዓለም ሞት ፍርድ የሚጠብቀው ሆነ፡፡

***ስለዚህ መዳን ማለት*** የሰው ዘር በቁጥጥር ስር አድርገውት ከነበሩት ጠላቶቹ ከሥራ ሕግ፣ ከኃጢአት ባርነት፣ ከእርግማንና፣ ከክፉ መናፍስት ተገዥነት ነጻ በመውጣት ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት መልሶ በመታረቅ፣ በኃጢአቱ ምክንያት ይጠብቀው ከነበረው የዘለዓለም ሞት ፍርድ በማምለጥ እግዚአብሔር አብ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ያዘጋጀለትን የዘላለም ሕይወትና በረከት መውረስ መቻል ነው፡፡

አንድ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን አምኖ ኃጢአቱን በመናዘዝ፣ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ደም አጥቦ በማንጻት እንዲቀበለው፣ በሕይወት መዝገብም እንዲጽፈው በልቡ አምኖ ሲጸልይ እግዚአብሔር አዲስ የሰው መንፈስ ስለሚሰጠው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር የተወለደና ከመንፈሳዊ ጠላቶቹ ሁሉና ከዘለዓለም ሞት ፍርድ የዳነ አዲስ ፍጥረት ይሆናል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ መሆኑንና በወዲያኛው ዓለም የሚከፍለው ዋጋ እጅግ አደገኛ መሆኑን ከተረዳ እግዚአብሔር በጸጋው ያቀረበለትን ከኃጢአቱ ውጤት ማምለጫ፤ ከዚህ በታች በተጠቀሰው ሁኔታ ቃሉን ከአፉ በማውጣት መጠየቅ (መጸለይ) ይኖርበታል፡፡

### *አጭር ጌታን ኢየሱስን በእምነት የመቀበል ጸሎት ምሳሌ፤*

ጌታ ኢሱስ ሆይ! እኔ የተለያየ ኃጢአት የፈጸምኩ በመሆኔ እግዚአብሔርን ስላሳዘንኩና ሰውን ስለ በደልኩ ይቅር በለኝ፡፡

ከኃጢአቴ ሁሉ በደምህ አጥበህ አንጻኝ፡፡ በሕይወት መዝገብህም ጻፈኝ፡፡

እኔም ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ኃጢዓትንና ዲያብሎስን ክጃለሁ፡፡

አንተንና ቅዱሱ ቃልህን በመከተል ለመኖር ቃል እገባለሁ፡፡

ደግሜ በኃጢአትና በጠላቴ እንዳልሰናከል ያንተ እርዳታ አይለየኝ፡፡ አሜን!!

*ይህ ጸሎት በጣም አጭር ቢሆንም ከልብ በሆነ እምነት ከተጸለየ ልብን በሚያየው አምላክ ፊት ተቀባይነት ያለውና ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔር የማዳን ጸጋ የሚያስገኝና መንፈሳዊ ሕይወትን ለመለወጥ መሰረት የሚሆን ነው።*

© ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.